# ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት

VOTE 2025

### *ከደሞዝዎ ምንም ሳይቆረጥ፡ ከግል ወይም ከዓመታዊ ዕረፍትዎ ሳይቀነስ ሂዶ ለመምረጥ ፍቃድ ማግኘት መብትዎ ነው።*

የሚመርጡበት ሰዓት ስራ ላይ ባሉበት ግዜ ከሆነ፡ ኣሰሪዎ ለመምረጥ ለሚያስፈልግዎ ግዜ ሊከፍሎት ይገባል። ኣሰሪዎ የግል ግዜዎን ወይም የዕረፍት ግዜዎን እንዲጠቀሙ ሊጠይቅዎ ኣይችልም።

ሂዶ ለመምረጥ የሚያስፈልጎትን ግዜ ብቻ ይውሰዱ። ከዛ በውሃላ ወደ ስራዎ ተመለሱ።

ኣስሪዎ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ ሂደው እንዲመርጡ ሊከለክልዎ፡ ወይም በዚህ መብት ጣልቃ ሊገባ ወይም ለመመረጥ በስንት ሰዓት ላይ መሄድ እንዳለቦ ሊመርጥልዎ ኣይችልም።

ኣሰሪዎ፡ በስንት ሰዓት ላይ ከምርጫው ቦታ እንደምትመለሱ ሊጠይቅ ይችላል። በተጨማሪም ስራ የሚደናቀፍበትን ግዜ ለማሳነስ፡ ሁሉም ሰራተኞች በኣንድ ግዜ እንዳይሄዱ ሊያሳስብ ይችላል።

በማንኛውም የመላው ኣገር፡ በክፍለሃገርና ግዜው በደንብ በታወቀ በኣካባቢ ምርጫዎች ላይ ለመሳተፍ ከስራ ፍቃድ የማግኘት መብት ኣሎት።

### የ2025 ቀናት

የማጣርያ ምርጫ
ማክሰኞ፡ ነሃሴ 12 ቀን

በኣካል ሳይገኙ የሚደረግ ምርጫ
በፖስታ መምረጥ ወይም በኣካል ተገኝተው የሚመረጥበት ቀን - ከመስከረም 19ቀን እስከ ህዳር 3 ቀን

ለመምረጥ ተመዝገቡ
በዋናው ምርጫ ቀን፡ ግዜ ለመቆጠብ ቀደም ብለው በግዜ እስከ ጥቅምት 14 ቀን ለመምረጥ ይመዝገቡ።

የምርጫ ቀን
ማክሰኞ ህዳር 4 ቀን

## *ቅሬታዎች*

ይህንን የምርጫ ህግ የሚያፈርስ ኣሰሪ፡ ሕግ በማፍረስ ኣነስተኛ ወንጀል ተከሳሽ ነው። ከሰራተኞች የሚነሳ ቅሬታ በቀበሌው ጠበቃ ጽሕፈት ቤት ሊመዘገብ ይገባል።

*ከበስተጀርባ ይቀጥላል...*

# ለመምረጥ ከስራ ፍቃድ ስለማግኘት

VOTE 2025

...ከበፊቱ ገጽ የቀጠለ

## በቀሪ የድምጽ መስጫ ቀድመው ድምፅ ይስጡ

በምርጫ ቀን ድምጽ መስጠት ካልፈለጉ ወይም ካልቻሉ ቀደም ብለው መምረጥ ይችላሉ። ምርጫው ከመድረሱ 46 ቀናት በፊት በሚጀመረው የቀሪ የድምፅ መስጫ ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ እንዲካተት ለምርጫ ከስራ እረፍት የማግኘት መብት የሚሰፋ ይሆናል።

በአካባቢዎ የምርጫ ቢሮ በቀሪ ድምጽ መስጫ ቀድመው ድምጽ መስጠት ይችላሉ። በ mnvotes.gov/absentee ላይ የቀሪ ድምጽ መስጫ ወረቀት በፖስታ እንዲላክልዎ መጠየቅ ይችላሉ።

**ለአሰሪዎ የሚሰጥ ደብዳቤ**

*ከስራ ወጥተው የመምረጥ መብት እንዳሎት ለአሰሪዎ የሚያስረዳና የሚሰጥ ደብዳቤ ለማግኘት mnvotes.gov ይጎብኙ።*